## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

# የንግድ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአደረጃጀትና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 968/2015

ግንቦት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 968/2015

# የንግድ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት ኦፐሬተር የአደረጃጀትና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጭነት ትራንስፖርት ኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 968/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) **"አዋጅ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 ነው።
2) **"የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ"** ማለትበጭነት ማመላለሻ ንግድ ሥራ ለመሰማራት በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ ለተገኘ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።
3) **"ደረጃ"** ማለት በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት ለተመዘገበኦፕሬተርየሚሰጥ ደረጃ ነው።
4) **"ኦፕሬተር"** ማለትአግባብነት ባለው የንግድ ሕግ መሠረት ተመዝግቦ በመንገድ ጭነት ማመላለሻ ስራ ላይ ለመሰማራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው እናበዚህ መመሪያ መሠረት የኦፕሬተርነትየብቃት ማረጋገጫ ፈቃድየተሰጠው ሰው ነው።
5) **"ስቲከር"** ማለት የኦፕሬተሩን ደረጃና የንግድ ስም የሚገልፅ እና በተሽከርካሪው አካል ላይ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ የሚለጠፍ መለያ ምልክት ነው።

6) **"ጭነት"** ማለት ማንኛውም በመንገድ ላይ በተሽከርካሪዎች ተጭኖ የሚጓጓዝ ደረቅ፣ ፈሳሽ ወይም ልዩ ጭነት ነው፡፡

7) **"የንግድ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት"**ማለት አግባብነት ባለው የንግድ ሕግ መሠረት ተመዝግቦ በሀገሪቱ መንገዶች ላይ በጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የሚሰጥ ማንኛውንም በዚህ መመሪያ የተሸፈነ ጭነት የማጓጓዝ አገልግሎት ነው፡፡

8) **"የግል ትራንስፖርት"** ማለት በአንድ የተፈጥሮ ሰው በግለሰብ ነጋዴነት የተቋቋመ የጭነት ትራንስፖርት ድርጅት ነው፡፡

9) **"የልዩ ጭነት ትራንስፖርት"** ማለት በቀላሉ ሊበላሹ ወይም ሊጎዱ የሚችሉ እና ለማጓጓዝ ልዩ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ጭነቶች በልዩ ጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፡፡

10) **"የልዩ ጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪ"**ማለት ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎችን፣ የተበላሹ ወይም አደጋ የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች ለመጫን ወይም ለመጎተት፣ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ጭኖ ለማጓጓዝ ታስቦ የተሰራ ተሽከርካሪ ሲሆን የአበባ፣ የአትክልት፣የፍራፍሬ፣ የቁም እንስሳና የስጋ ምርቶችን እና ሎሎች ከመደበኛ ጭነት በተለየ ሁኔታ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ጭነቶችን በመደበኛነት ለማጓጓዝ የሚያስችሉ አካሎች የተገጠሙለት ተሽከርካሪን ይጨምራል፡፡

11) **"የተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር አስተዳደር ሥርዓት"** ማለት የኦፕሬተሮችን ዝርዝር መረጃ ማለትም፡-የንግድ ስም፣ የንግድ ምዝገባ ቁጥር፣የኦፐሬተሩን የንግድ አደረጃጀት ዓይነት፣ የኦፕሬተርነት ምዝገባ ቁጥርና ደረጃ፣የኦፐሬተሩን የተሽከርካሪ ዓይነት እና የአሽከርካሪ ማንነት ለመለየት የሚያስችል ዝርዝር መረጃ ለመመዝገብ እና ለመቆጣጠር የሚያስችል በሚኒስቴሩ የለማ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ነው፡፡

12) **"የኪራይ ውል"** ማለት ሰነዶችንለማረጋገጥና ለመመዝገብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የጭነት ተሽከርካሪየኪራይ ውል ነው፡፡

13) **"ዴስክ"**ማለት በሚኒስቴሩ ውስጥ የተዋቀረና ለኦፕሬተሮች የጭነት ትራንስፖርትን የሚመለከቱ አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን የሚሰጥ በሎጂስቲክስ አገልግሎት ሬጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ስር የሚገኝ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ዴስክ ነው፡፡

14) **"የሎጂስቲክስ አገልግሎት እና ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈጻሚ"** ማለት በሚኒስቴሩ ውስጥ የተዋቀረና ኦፕሬተሮች ማንኛውንም በዚህ መመሪያ የተሸፈነ አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚያገኙበት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን በሚኒስቴሩ ውስጥ የአደረጃጀት ለውጥ ቢደረግ እንኳ ይህን ተግባር የሚያከናውነው መምሪያ ነው፡፡

15) **"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

16) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፡፡

17) በአዋጁ አንቀጽ 2 ላይ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት እና ሐረጎች በዚህ መመሪያ ላይም ተፈጻሚነትአላቸው፡፡

18)በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የንግድ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ከሚኒስቴሩ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተሰጠው ማንኛውም ኦፕሬተር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የተፈቀደላቸው የጭነት መጠን ከ70 ኩንታል ወይም 7 ቶን በታች የመጫን አቅም ባላቸው ተሽከርካሪዎች ለሚደራጁ የንግድ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 4. <u>የመመሪያው ዓላማዎች</u>

መመሪያው ተከታዮቹ ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) ግልፅናየጠራየኦፕሬተር አደረጃጀት ሥርዓትን በመዘርጋት በቴክኖሎጂ ውጤቶች የታገዘ ጠንካራና ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥና የቁጥጥር ሥርዓትን የሚከተሉ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮችን ማፍራት፤

2) አዳዲስባለሀብቶችወደዘርፉየሚገቡበትንሁኔታበማመቻቸትየአገልግሎቱንቀጣይነትማረጋገጥ፤

3) በዘርፉ ከፍተኛ አቅምና ብቃት ያላቸውን ኦፕሬተሮች በመፍጠር በመካከላቸው ያለውን ውድድር ከፍ ማድረግና የተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት ጭነቶች ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ እንዲጓጓዙ ማስቻል፤

4) የልዩ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮችን በማበረታታትአገልግሎቱን ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ምቹሁኔታንመፍጠር፤

5) የሀገራችን ኦፕሬተሮች አሠራር፣ ብቃት እና አደረጃጀት ዘመናዊ ጠንካራ ቁጥጥር በማድረግ በአፍሪካ በሚኖረው ቀጠናዊ እና የሁለትዮሽ የትራንስፖርት ትስስር ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማስቻል ነው።

## ክፍል ሁለት

## ስለኦኘሬተር የወል ድንጋጌዎች

5. ማንኛውም ኦፐሬተር የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1) በባለቤትነትና በኪራይ ያስመዘገባቸውን ተሽከርካሪዎች፣ በጭነት ተሽከርካሪዎቹ የተሸፈነ የጉዞ ርቀት፣ የተጓጓዘ ጭነት መጠን፣ የሰው ኃይልና የቢሮ አደረጃጀት፣ ወቅታዊ የጭነት ማጓጓዣ የገበያ ዋጋ /ታሪፍ/ መረጃ እና ሌሎች መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝናበየወሩ የመጨረሻዎቹ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፤

2) የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሚያስችል ግልጽ ዕቅድ በማዘጋጀት አተገባበሩንና አፈጻጸሙን የሚመለከት ሪፖርት በየስድስት ወር ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፤

3) በሚኒስቴሩ ወይም በመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት አማካኝነት በሚከናወኑ የመንገድ ደህንነት ማሻሻያ ተግባሮች ላይየመሳተፍ፤

4) የተለየ ስምምት ከሌለ ወይም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካልገጠመው በስተቀር ለማጓጓዝ የተረከበውን ጭነት ከአስጫኙ ጋር በተፈራረመው ውል መሰረት የማጓጓዝ፤

5) ሚኒስቴሩ ባወጣዉ ዝርዝር መስፈርት መሰረት የተዘጋጀና የድርጅቱን ስም እና አርማ የያዘ ስቲከር በጭነት ተሽከርካሪዎቹ ጋቢና በሮች ውጫዊ አካል ወይም በሁለቱም የተሽከርካሪው ቀኝና ግራ ጎኖች ላይ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ የመለጠፍ፤

6) በተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር አስተዳደር ሥርዓት ያስመዘገባቸው ተሽከርካሪዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ በሚሆኑበት ጊዜ ለዴስኩ በዕለቱ የማሳወቅ፤

7) በተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ኦፐሬተሮች አስተዳደር ሥርዓት ላይ በተመዘገቡት የጭነት ተሽከርካሪዎቹ ብቻ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት የመስጠት፤

8) በተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ኦፐሬተሮች አስተዳደር ሥርዓት ያስመዘገባቸውን ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ስርዓት የመዘርጋትና ለቁጥጥር እንዲያመች በቀን ለ24 ሰዓትና በሳምንት ለ7 ቀናት የቴክኖሎጂ ስርዓቱን ለሚኒስቴሩ ክፍትና ተደራሽ የማድረግ፤

9) በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ (8) የተጠቀሰውየቴክኖሎጂ ስርዓት ሲበላሽ በዕለቱ ለዴስኩ የማሳወቅ እና ብልሽቱን አስተካክሎ በዕለቱ ለዴስኩ የማሳወቅ፤

10) በወደብ ላይ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ጭነትን በአስቸኳይ ለማንገንዝ በመንግስት በሚፈለግበት ጊዜ በሚኒስቴሩ በሚሰጥ የኮታ ድልድል መሰረት ጭነቶችን የማንጓዝ፤

11) ለዚህ መመሪያ አተገባበር በኪራይ ይዞ ለሚገለገልባቸው የጭነት ተሽከርካሪዎች እና አሽከርካሪዎቻቸው እንደባለቤት እና አሰሪ ሆኖ ሙሉ ኃላፊነቱን የመውሰድ፤

12) በኪራይየያዛቸው የጭነት ተሽከርካሪዎች የኪራይ ውል ሲቋረጥ ውሉ በተቋረጠ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ለዴስኩ የማሳወቅ፤

13) አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን በወቅቱ የማሳደስ፤እና

14) የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ሕጎችን፣ህግን መሠረት በማድረግ በሚኒስቴሩ የሚወጡ ማኑዋሎችንና አሰራሮችን አክብሮ በተሰጠው የኦፐሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።

6. ሚኒስቴሩ በማንኛውም ጊዜ ኦፐሬተሩ በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ግዴታዎቹን በአግባቡ እየተወጣ ለመሆኑ ቁጥጥር ያደርጋል፤

7. ኦፐሬተሩ በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ግዴታዎቹን በአግባቡ እንዲወጣ የሚረዱ ተግባሮች ካሉ ሚኒስቴሩ በህግ አግባብ ለኦፐሬተሩ እገዛዎች ሊያደርግ ይችላል፤

## ክፍልሦስት

## ስለኦፕሬተርነት ፈቃድ

### 8. የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሰነዶች

የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም አመልካች፡-

1) የኦፕሬተሩ አድራሻ፡-

ሀ. የሚገለገልበት ቤት የአመልካቹ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፤

ለ. የሚገለገልበት ቤት የኪራይ ከሆነ የኪራይ ዘመኑ ያላለፈበት እና በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ የኪራይ ውል፤

ሐ. የኪራይ ቤቱ የመንግስት ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኪራይ ውል፤

2) በዚህ መመሪያመሠረት የተቀመጠው የሰው ኃይል የቅጥር ውል፣ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ እና የትምህርት ማስረጃ፤

3) የተሽከርካሪውየባለንብረትነት ማረጋገጫ ደብተር፣የተሽከርካሪው የቴክኒክ ምርመራ የምስክር ወረቀት፣ የተሽከርካሪውየ3ኛ ወገን መድን፣ የንግድ ምዝገባ ፈቃድ፣የጸና የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፣ የአሽከርካሪዎቹ የታደሰ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫና የቅጥር ውል፣ አስፈላጊ ከሆነ የረዳትየታደሰ መታወቂያና የቅጥር ውል፤

4) ሁሉም ተሽከርካሪዎች ሚኒስቴሩ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት የሚሰጥ ጂፒኤስ የተገጠመላቸው መሆኑን የሚገልጽ ህጋዊ መረጃ፤ እና

5) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ሰነዶቹ ኦሪጂናል መሆናቸውንና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ በተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት አስተዳደር ስርዓት በመጠቀም አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

## 9. የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ

1) አግባብነት ባለው ህግ መሠረት የአክስዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ድርጅት አቋቁመው የንግድ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ የትራንስፖርት ድርጅቶች በዚህ መመሪያ መሠረትለድንበር ተሻጋሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ትራንስፖርት አገልግሎት በደረጃ አንድ እና ደረጃ ሁለት ባሉት አደረጃጀቶች በሚያሟሉት መስፈርት መሠረት ተደራጅቶ የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት ተደራጅቶ የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም አመልካች ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፤

3) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚጠየቅ የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማመልከቻ በመመሪያው ውስጥ የተጠቀሱትን መረጃዎችና አባሪ ሰነዶች አሟልቶ መቅረብ አለበት፤

4) ሚኒስቴሩ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድየቀረቡትን ሰነዶች ትክክለኛነት በማረጋገጥና እና በዚህ መመሪያ መሠረት የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸውን በመመዘንና አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የኦፐሬተርነት ብቃት ማጋገገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ሚኒስቴሩ የኦፐሬተርነት ብቃት ማጋገጫ ፈቃድ ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገው ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት በመጥቀስ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ መልስ ይሰጣል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እናበዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 11 እስከ 15የተገለፀው በሚኒስቴሩ የሚሰጠው የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተሽከርካሪዎች ዕድሜ፣ ብዛት እና የመጫን አቅም መሠረት ይወሰናል፡፡

7) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተገለጹት የአደረጃጀት ዓይነቶችውጭ የትራንስፖርት የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ ማመልከቻ ይዘው ለሚመጡ

አመልካቾችበዚህ መመሪያ ለአክስዮን ማኅበር በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡

## 10. የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዓይነቶች

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጡ የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች፡-

ሀ. የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤

ለ. የልዩ ጭነት ትራንስፖርት የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና

ሐ. የፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ናቸው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፡

ሀ. ደረጃ 1 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤

ለ. ደረጃ 2 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤

ሐ. ደረጃ 3 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤

መ. ደረጃ 1 የሀገር ውስጥ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣

ሠ. ደረጃ 2 የሀገር ውስጥ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣

## 11. የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት አክስዮን ማኅበር የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

### 1) የድንበር ተሻጋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

ሀ. ደረጃ 1 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ የመነሻ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 5፣ በሁለተኛው ዓመት 10 ፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 25 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ30 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. ከ1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. ከ1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያስገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## ለ. <u>ደረጃ 2 የድንበር ተሻጋሪ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ የመነሻ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 3፣ በሁለተኛው ዓመት 5፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 15 ተሽከርካሪዎችን ማሟላት አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ20 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ20 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁጥር 1-3የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያስገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## ሐ. <u>ደረጃ 3 የድንበር ተሻጋሪ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ የመነሻ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 7 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ20 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሐ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያስገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 2) የሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

### ሀ. ደረጃ 1 የሀገር ውስጥ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ የመነሻ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 2፣ በሁለተኛው ዓመት 5፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 10 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ25 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ ፊደል /ሀ/ ተራ ቁጥር 1-3የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያስገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

### ለ. ደረጃ 2 የሀገር ውስጥ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት

1/ የመነሻ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 5 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፣

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ ፊደል /ለ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 12. ለደረቅ ጭነት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

### 1) የድንበር ተሻጋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

#### ሀ. ደረጃ 1 የድንበር ተሻጋሪ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 3፣ በሁለተኛው ዓመት 7፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 15 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ30 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ ፊደል /ሀ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## ለ. ደረጃ 2 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ የተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 2፣ በሁለተኛው ዓመት 4፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 7 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ20 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ20 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ ፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ ፊደል /ለ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## ሐ. ደረጃ 3 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 2፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 4 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ20 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሐ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 2) የሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

### ሀ. ደረጃ 1 የሀገር ውስጥ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 2፣ በሁለተኛው ዓመት 5፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 10 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ25 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

### ለ. ደረጃ 2 የሀገር ውስጥ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሦስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 5 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፣

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ 7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ለ/ ከተራ ቁጥር1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 13. የደረቅ ጭነት የግል ትራንስፖርት ኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

### 1) የድንበር ተሻጋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

#### ሀ. ደረጃ 1 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 3፣ በሁለተኛው ዓመት 5፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 7 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ30 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁጥር 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ኦፐሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

#### ለ. ደረጃ 2 የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 2፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 4 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ20 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ20 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ኦፐሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

### ሐ. <u>ደረጃ 3 የድንበር ተሻጋሪ የግል ትራንስፖርት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ በባለቤትነት የያዘው መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት 1 መሆን አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ20 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሐ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ኦፐሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 2) የሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

### ሀ. <u>ደረጃ 1 የሀገር ውስጥ የግል ትራንስፖርት የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 2፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 5 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ ጭነት ማመላሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ መያዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ ኦፕሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

### ለ. <u>ደረጃ 2 የሀገር ውስጥ የግል ትራንስፖርት የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ በባለቤትነት የያዘው መነሻ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት 1 መሆን አለበት፡፡

2/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው እድሜ ያለገደብ ነው፡፡

3/ የእያንዳንዱ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ ኦፕሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 14. <u>የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

### 1) የድንበር ተሻጋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

### ሀ. <u>የድንበር ተሻጋሪ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር የኦፕሬተር ብቃትማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ መነሻ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 7 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ30,000 ሊትር ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ30,000 ሊትር ያላነሰ ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ ሊይዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ30,000 ሊትር ያላነሰ ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

ለ. <u>የድንበር ተሻጋሪ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ መነሻ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 4 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ30,000 ሊትር ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4) ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ30,000 ሊትር ያላነሰ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ ሊይዝ ይችላል፡፡

5) ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ30,000 (ሰላሳ ሽ) ሊትር ያላነሰ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

ሐ. <u>የድንበር ተሻጋሪ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ የግል ትራንስርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ በባለቤትነት የያዘው መነሻ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት 1 መሆን አለበት፡፡

2/ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው እድሜ ያለገደብ ነው፡፡

3/ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው የመጫን አቅም ከ30,000 ሊትር ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሐ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ከ1 እስከ 5 የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ በስማቸው ያላቸው ባለንብረቶች እስከ 25 የሚደርሱ፤ ከ6 እስከ 10 የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ በስማቸው ያላቸው ባለንብረቶች እስከ 50 የሚደርሱ፤ እንዲሁም ከ11 በላይ የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ በስማቸው ያላቸው ባለንብረቶች ደግሞ እስከ 100 የሚደርሱ እና የመጫን አቅማቸው ከ30,000 ሊትር ያላነሰ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 2) የሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

ሀ. <u>የሀገር ውስጥ ፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኀበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/መነሻ የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሦስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 5 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራቁ. 1 እና2 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ ሊይዝ ይችላል፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራቁ. 1 እና2 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ያልተገደበ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

ለ. <u>የሀገር ውስጥ ፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ መነሻ የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 2፣ በሦስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 3 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹዕድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1 እና2 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ ሊይዝ ይችላል፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራቁ. 1 እና2 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ያልተገደበ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

ሐ. <u>የሀገር ውስጥ ፈሳሽ ጭነት የግል ትራንስርት የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ በባለቤትነት የያዘው መነሻ የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ ብዛት 1 መሆን አለበት፡፡

2/ የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪውእድሜ ያለገደብ ነው፡፡፡፡

3/ ከላይ በፊደል /ሐ/ ተራቁ. 1 እና2 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪዎችን ያለዕድሜ ገደብ ኦፐሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 15. የልዩ ጭነት ትራንስፖርት የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

### 1) የድንበር ተሻጋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

#### ሀ. የድንበር ተሻጋሪ የልዩ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ የመነሻ ልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 7 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

#### ለ. የድንበር ተሻጋሪ የልዩ ጭነት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1/ የመነሻ ልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 4 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

ሐ. <u>የድንበር ተሻጋሪ የልዩ ጭነት የግል ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1) በባለቤትነት የያዘው የመነሻ ልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት 1 መሆን አለበት፡፡
2) የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3) የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
4) ከላይ በፊደል /ሐ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ኦፕሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 2) የሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፡-

ሀ. <u>የሀገር ውስጥ ልዩ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድመስፈርት</u>

1/ መነሻ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 3፣ በሦስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ5 ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡
2/ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3/ የእያንዳንዱ ልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ያልተገደበ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ ሊይዝ ይችላል፡፡
5/ ከላይ በፊደል /ሀ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ያልተገደበ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

ለ. <u>የሀገር ውስጥ ልዩ ጭነት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ መነሻ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት በመጀመሪያው ዓመት 1፣ በሁለተኛው ዓመት 2፣ በሦስተኛው ዓመት ደግሞ ቢያንስ 3ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት መያዝ አለበት፡፡

2/ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ የእያንዳንዱ ልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ያልተገደበ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ተጨማሪ አድርጎ ሊይዝ ይችላል፡፡

5/ ከላይ በፊደል /ለ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ያልተገደበ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ያለገደብ ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

ሐ. <u>የሀገር ውስጥ የልዩ ጭነት የግል ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>

1/ መነሻ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት 1 መሆን አለበት፡፡

2/ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እድሜ ያልተገደበ ነው፡፡

3/ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው የመጫን አቅም ከ7 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

4/ ከላይ በፊደል /ሐ/ ተራ ቁ. 1-3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች ዕድሜያቸው ያልተገደበ እና የመጫን አቅማቸው ከ7 ቶን ያላነሰ የልዩ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ኦፕሬተሩ በስሙ ካስመዘገበው ሁለት ዕጥፍ ያህል ተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን በተረጋገጠ የኪራይ ውል ይዞ ሊገለገል ይችላል፡፡

## 16. ለግል ንግድ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

1) በባለቤትነት የያዘው መነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 1 መሆን አለበት፡፡
2) የተሽከርካሪው እድሜ ያለገደብ ነው፡፡
3) የተሽከርካሪው የመጫን አቅም ከ 20 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣

## 17. በኪራይ ስለሚመዘገብ ተሽከርካሪ

1) ተሽከርካሪ በኪራይ የሚይዝ ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚከራያቸው ተሽከርካሪዎች ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ወይም የወሰዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡
2) ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለንብረት የሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ ተሽከርካሪውን ለሌላ ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚያከራይ ከሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2፣ እንዲሁም በአንቀጽ 19 እና 20 የተቀመጡትን መስፈርቶች እንዲያሟላ አይገደድም፡፡
3) በሁሉም አደረጃጀት እና የትራንስፖርት ዓይነቶች የሚደረገው የኪራይ የቆይታ ጊዜ ቢያንስ ለአንድ ዓመት መሆን አለበት፡፡
4) በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 11 እስከ 15 እንደተደነገገው በኪራይ ከተፈቀደው የተሽከርካሪ ቁጥር በተጨማሪ ጎታች መኪና ኖሮት ተሳቢ ከሌለው ወይም ተሳቢ ኖሮት ጎታች መኪና የሌለው ኦፐሬተር በስሙ ካስመዘገበው ጎታች መኪና ጋር የሚጣመር ተሳቢ ወይም በስሙ ካስመዘገበው ተሳቢ ጋር የሚጣመር ጎታች መኪና ቢያንስ ለአንድ ዓመት በሚቆይ የኪራይ ውል በተጨማሪነት አስመዝግቦ መጠቀም ይችላል፡፡
5) በአከራይ እና በኦፐሬተሩ መካከል የተፈፀመው የኪራይ ውል የቆይታ ጊዜው ሳያልቅ ከተቋረጠ ኦፐሬተሩ በ7 የስራ ቀናት ለዴስኩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
6) ማንኛውም ተሽከርካሪን በኪራይ የያዘ ኦፐሬተር በተከራየው ተሽከርካሪ አካል ላይ በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተጠቀሰው ከራሱ መደበኛ ስቲከር በተጨማሪ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ ልዩ ስቲከር እንዲለጠፍ ማድረግ አለበት፡፡
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (6) መሠረት በኪራይ ተሽከርካሪው ላይ የሚለጠፈው ልዩ ስቲከር ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው መስፈር መሰረት ይሆናል፡፡

## 18. የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአገልግሎት ወሰን

1) በድንበር ተሻጋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት በደረጃ 1 ወይም በደረጃ 2 ወይም በደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተርበሀገር ውስጥ እና በዓለም-አቀፍ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
2) በሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት በደረጃ 1 ወይም በደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተር በሀገር ውስጥ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
3) ለግል ንግድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተመዘገበ ድርጅት የራሱን ምርት ወይም ግብዓት ብቻ በራሱ ተሽከርካሪ በሀገር ውስጥ እና በዓለም-አቀፍ መስመሮች ላይ የሚያጓጉዝ ይሆናል፡፡

## 19. የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ

1) በድንበር ተሻጋሪ ደረቅ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሀ" እና "ለ" መሠረትይሆናል፡፡
2) ለሀገር ውስጥ ደረቅ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ሥራ አስኪያጅ፣ 1 ኦፕሬሽን ባለሙያ እና 1 የሒሳብ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ይሆናል፡፡
3) በልዩ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ሥራ አስኪያጅ ፣ 1 ኦፕሬሽን ባለሙያ እና 1 የሒሳብ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ይሆናል፡፡
4) በፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ሥራ አስኪያጅ ፣ 1 ኦፕሬሽን

## 18. የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአገልግሎት ወሰን

1) በድንበር ተሻጋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት በደረጃ 1 ወይም በደረጃ 2 ወይም በደረጃ 3 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተርበሀገር ውስጥ እና በዓለም-አቀፍ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
2) በሀገር ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት በደረጃ 1 ወይም በደረጃ 2 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ኦፕሬተር በሀገር ውስጥ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
3) ለግል ንግድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተመዘገበ ድርጅት የራሱን ምርት ወይም ግብዓት ብቻ በራሱ ተሽከርካሪ በሀገር ውስጥ እና በዓለም-አቀፍ መስመሮች ላይ የሚያንጓጉዝ ይሆናል፡፡

## 19. የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ

1) በድንበር ተሻጋሪ ደረቅ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሀ" እና "ለ" መሠረትይሆናል፡፡

2) ለሀገር ውስጥ ደረቅ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ሥራ አስኪያጅ፣ 1 ኦፕሬሽን ባለሙያ እና 1 የሒሳብ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ይሆናል፡፡

3) በልዩ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ሥራ አስኪያጅ ፣ 1 ኦፕሬሽን ባለሙያ እና 1 የሒሳብ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ይሆናል፡፡

4) በፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ሥራ አስኪያጅ ፣ 1 ኦፕሬሽን



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

ባለሙያ እና 1 የሒሳብ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ማሟላት ያለበት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ይሆናል፡፡

5) ከ5 ተሽከርካሪ በታች በመያዝ በግል ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ኦፕሬተር ቢያንስ 1 ስራ አስኪያጅ እና 1 ሒሳብ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ "ለ" የተቀመጠው የትምህርት ደረጃ፣ የትምሕርት ዓይነትና የሥራ ልምድ አስገዳጅ አይሆንበትም፡፡

6) ሚኒስቴሩ በማንኛውም ጊዜ በሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር የአንድ ድርጅት የሰው ኃይል አደረጃጀት የኦፕሬተርነት ፈቃድ የተሰጠበትን አገልግሎት ለመስጠት በማያስችለው ደረጃ ላይ መሆኑን ካረጋገጠ ለድርጅቱ የተሰጠውን ደረጃ ሊቀንስ ወይም ለድርጅቱ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

7) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ6 የተመለከተውን እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ለድርጅቱ የሰው ኃይል አደረጃጀቱን እንዲያስተካክል ከአንድ ወርያልበለጠ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 20. ስለኦፕሬተሩ የንግድ ሥራ መለያዎች

ማንኛውም ኦፕሬተር፡-

1) አድራሻው በግልፅ የሚታወቅ ቢሮ ሊኖረው ይገባል፡፡
2) ክብ ማኅተም ሊኖረው ይገባል፡፡
3) የድርጅቱን ስም፣ አርማ እና አድራሻ የያዘ ስቲከር ማሳተምና በዚህ መመሪያ መሠረት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው ጋቢና ላይ መለጠፍ አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ /3/ የተጠቀሰው እና ማንኛውም ኦፕሬተር ለደረጃው የተቀመጠውን ቀለም የያዘ ስቲከር የመለጠፍ ግዴታ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የስቲከሩ መደብ እና የጽሑፉ ቀለም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**ሀ/ ለደረጃ አንድ(ለግል ትራንስፖርት፣ለአክሲዮን ማኅበር ወይም ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር)** የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርጽ እና መጠን፡-

- ሙሉ ክብ ሆኖ 30 ሣ.ሜ በ30 ሣ.ሜ የሆነ፤

- የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡- አረንጓዴ፤
- የጽሑፉ ቀለም፡- ነጭ፤
- የጽሑፉ ቋንቋ፡- አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የድርጅቱን አድራሻ የሚገልፅ እና በተጨማሪም የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ሎጎ በስቲከሩ ግራና ቀኛ ያለው መሆን አለበት፡፡

**ለ/ ለደረጃ ሁለት (ለግል ትራንስፖርት፣ለአክሲዮን ማኅበር ወይም ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር)** የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርጽ እና መጠን፡-

- ሙሉ ክብ ሆኖ 30 ሣ.ሜ በ30 ሣ.ሜ የሆነ፤
- የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡- ቢጫ፤
- የጽሑፉ ቀለም፡- ጥቁር፤
- የጽሑፉ ቋንቋ፡- አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የድርጅቱን አድራሻ የሚገልፅ እና በተጨማሪም የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ሎጎ በስቲከሩ ግራና ቀኛ ያለው መሆን አለበት፡፡

**ሐ/ ለደረጃ ሦስት (ለግል ትራንስፖርት፣ለአክሲዮን ማኅበር ወይም ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር)** የሚሰጥ ስቲከር የስቲከሩ ቅርጽ እና መጠን፡-

1. ሙሉ ክብ ሆኖ 30 ሣ.ሜ በ30 ሣ.ሜ የሆነ፣
2. የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡- ቀይ፣
3. የጽሑፉ ቀለም፡- ነጭ፣
4. የጽሑፉ ቋንቋ፡- አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የድርጅቱን አድራሻ የሚገልጽ እና በተጨማሪም የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ቤቱ ሎጎ በስቲከሩ ግራና ቀኛ ያለው መሆን አለበት፡፡

**መ/ በኪራይ ለሚመዘገብ ተሽከርካሪ፡- (ለግል ትራንስፖርት፣ለአክሲዮን ማኅበር ወይም ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር)** የሚሰጥ ልዩ ስቲከር፡-

1. የስቲከሩ ቅርጽ እና መጠን፡- ባለ ሶስት ጎን ሆኖ ሁሉም ጎኖች 20 ሣ.ሜ የሆነ፣
2. የስቲከሩ የመደብ ቀለም፡- ሰማያዊ፣
3. የጽሑፉ ቀለም፡- ጥቁር፣
4. የጽሑፉ ቋንቋ፡- አማርኛ እና እንግሊዝኛ ሆኖ የአከራዩን አድራሻ የያዘ መሆን አለበት፡፡

## 21. የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዕድሳት

መስፈርቱን አሟልቶ ከሚኒስቴሩ የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ኦፕሬተር፡-

1) በየዓመቱ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፡፡
2) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ የተቀመጡትን መስፈርቶች በዕድሳት ወቅትም አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

## 22. የደረጃ ማሻሻያ እና ክለሳ

1) በዚህ መመሪያ መሠረት ደረጃ የተሰጠው ኦፕሬተር ለተመዘገበበት ደረጃ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ካሻሻለ ወይም ካጓደለ ሚኒስቴሩ የኦፕሬተሩን ደረጃ በዚሁ ለውጥ መሰረት ሊያሳድግ ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡
2) በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 11 እስከ 15 ድንጋጌዎች በተመለከቱት መስፈርቶች ለአደረጃጀት ዓይነት እና ደረጃ የተቀመጠውን የመነሻ ተሽከርካሪ ብዛት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሠረት ኦፕሬተሩ አሟልቶ ካልተገኘ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

# ክፍል አራት

# የአደረጃጀት እና የሀብት ሽግግር ሂደት አፈጻጸም

## 23.የአደረጃጀት እና የሽግግር ሂደት አፈጻጸም

1) በቀድሞ የትራንስፖርት አዋጅ 468/1997 መሠረት ፈቃድ ወስደው በስራ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 መሠረት ተሽከርካሪዎቻቸውን በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት እንደገና በማስመዝገብ አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፡፡

2) በቀድሞ የትራንስፖርት አዋጅ 468/1997 መሠረት የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወስደው በሥራ ላይ የሚገኙ የትራንስፖርት ማኅበራት አግባብነት ባለው የንግድ

ህግ መሠረት በንግድ አደረጃጀት ተመዝግበውና ተገቢውን የንግድ ፈቃድ ይዘው በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት አዲስ በተመዘገቡበት የአክስዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም የግል ትራንስፖርት ስም አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት እንደገና ተመዝግበው የኦፕሬተርነት ፈቃድ መውሰድ ያለባቸው ይህ መመሪያ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ዕለት ጀምሮ በሠላሳ /30/ የስራ ቀናት ውስጥ ይሆናል፤

4) በዚህ አንቀጽ መሠረት እንደገና ምዝገባ አድርገው አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያልወሰዱ ኦፕሬተሮች በንዑስ-አንቀጽ (3) ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ ቀድሞ የነበራቸው የኦፕሬተርነት ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አዲስ በሚለወጡበት የንግድ አደረጃጀት መሰረት ምዝገባ አድርገው አዲስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ያልወሰዱ ማኅበራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ ሕጋዊ ሰውነት አይኖራቸውም፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (4) እና (5) መሠረት የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ የተሰረዘና ሕጋዊ ሰውነቱን ያጣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ወይም ማኅበር ቀደም ሲል ከ3ኛ ወገን ጋር የነበረው የውል ወይም ሌላ ዓይነት ግንኙነት አግባብነት ባለው ህግ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 24. የማኅበራት የሀብት ሽግግር ሂደት አፈጻጸም

1) በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሰረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ የነበሩ የትራንስፖርት ማኅበራት ያላቸውን ሀብትና ንብረት በገለልተኛ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ በማስመርመር በጠቅላላ ጉባኤው ማጸደቅ አለባቸው፡፡

2) በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ የነበሩ ማኅበራት ፈርሰው ያላቸው ሀብት እና ንብረት በአዲስ ወደ ሚቋቋሙበት የንግድ ድርጅት በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች መሠረት ይተላለፋል፡፡

3) ከማኅበር ወደ ንግድ ድርጅት የሚተላለፈው ሀብትና ንብረት ለማኅበሩ አባላት በግል ማከፋፈል የተከለከለ ነው፡፡

4) የቀድሞው ማህበር የሀብት እና ንብረት ዝውውር የሚመለከታቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በሚደረገው የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ጊዜ በማኅበሩ



of Ethiopia
Transport and Logistics

ስር ታቅፈው የሚገኙ አባላትን እና አዲስ በተቋቋመው የንግድ ድርጅት ውስጥ ባለድርሻ ሆነው የቀጠሉ አባላትን ብቻ ነው፡፡

5) በአዋጁ አንቀጽ 11 (7) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት የማኀበሩን ሀብት እና ንብረት አዲስ ወደሚቋቋመው የንግድ ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (3) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ማስተላለፍ ካልተቻለ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

6) በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ የነበሩ ማኀበራት ከሌላ ሦስተኛ ወገን ጋር የነበራቸው መብትና ግዴታ በዚህ መመሪያ መሠረት ከተመዘገቡበት ዕለት ጀምሮ አዲስ ወደተመሰረተው የንግድ ድርጅት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከተው ድንጋጌ የማኀበር አባላት በግል ከሌላ ሦስተኛ ወገን ጋር ያላቸው የመብትና ግዴታ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 25. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

ለማንኛውም ኦፕሬተር የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

1) የሌላ ኦፐሬተርን አርማና ስቲከር በማንኛውም ሁኔታ መገልገል፤
2) ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተባባሪ መሆን እና ስደተኞችን በተሽከርካሪው ደብቆ ማጓጓዝ፤
3) የኮንትሮባንድ እቃ ማጓጓዝ፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት፤
4) ባልተመዘገቡ፣ የብቃት ማረጋገጫ ባልወሰዱና ባላደሱ ወይም በታገዱ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት መስጠት፤
5) ትክክለኛ ያልሆኑና ሐሰተኛ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤
6) ከሚኒስቴሩ የተፈቀደለትን ስቲከርና ሌሎች ከኦፐሬተርነት ጋር የተያያዙ ፈቃዶች ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት፤
7) ሌሎች ሕገ-ወጥ ተግባራትን መፈጸም፤

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 26. የአሠራርና የሥነ-ምግባር ጉድለት የቅጣት አወሳሰን

በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የወጡ ሌሎች ሕጎችና ደንቦች ተፈፃሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የተመለከተውን አጠቃላይ የአሠራር እና ሥነ-ምግባር ጉድለቶችን በመፈጸም ኃላፊነትና ግዴታን በትክክል ባልተወጣ ማንኛዉም ኦፕሬተር የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

### 27. የአስተዳደራዊ ቅጣት እርከን

1) በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩት የአሠራር እና ሥነ-ምግባር ግድፈቶች በተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ አሽከርካሪዎች፣ በድርጅት ሠራተኞች ለሚፈፀሙ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ኦፕሬተሩ ኃላፊ ይሆናል።
2) ማንኛዉም የጭነት ትራንስፖርት ድርጅት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሐ" በእርከን አንድ እና ሁለት ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ፡-

ሀ/ በዕርከን አንድ ለተዘረዘሩ ጥፋቶች የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ

1) ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤
2) ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 30 ነጥብ ከደረሰ ከማንኛዉም አገልግሎት ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፐሬተሩ ተሽከርካሪ ለአንድ ወር ከሥራ ይታገዳል፣
3) ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 50 ነጥብ ከደረሰ ከማንኛዉም አገልግሎት ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፐሬተሩ ተሽከርካሪ ለሦስት ወር ከሥራ ይታገዳል፣
4) ለአራተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 70 ነጥብ ከደረሰ ጥፋቱ የተፈጸመመበት የኦፐሬተሩ ተሽከርካሪ ለስድስት ወራት ከሥራ ይታገዳል፤

5) ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ከቀጠለ ወይም የጥፋቱ ሪከርድ 90 ነጥብ ከደረሰ የኦፐሬተሩ ተሽከርካሪ ለአንድ ዓመት ከሥራ ይታገዳል፤

ለ/ **በዕርከን ሁለት ለተዘረዘሩ ጥፋቶች የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ**

1) ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤
2) ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 20 ነጥብ ከደረሰ ከማንኛውም አገልግሎት ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፐሬተሩ ተሽከርካሪ ለአንድ ወር ከሥራ ይታገዳል፣
3) ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 40 ነጥብ ከደረሰ ከማንኛውም አገልግሎት ጥፋቱ የተፈጸመበት የኦፐሬተሩ ተሽከርካሪ ለሦስት ወር ከሥራ ይታገዳል፣
4) ለአራተኛ ጊዜ ከሆነ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 60 ነጥብ ከደረሰ ጥፋቱ የተፈጸመመበት የኦፐሬተሩ ተሽከርካሪ ለስድስት ወራት ከሥራ ይታገዳል፤
5) ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ከቀጠለ ወይም የጥፋት ሪከርዱ 80 ነጥብ ከደረሰ የድርጅቱ የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ለ3 ወራት ከሥራ ይታገዳል፤
6) ማንኛውም ኦፐሬተር በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት አስቸኳይ ለሆኑና ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ለሆኑ በመንግስት የሚሰጡ የጭነት ትዕዛዞች አለመተባበር ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ኦፐሬተሩ ተሽከርካሪዎች በቀጥታ ለ6 ወራት ከሥራ ይታገዳሉ፡፡

## 28. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1) በመመሪያው መሠረት በተሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ቅሬታውን አገልግሎቱን ለሚሰጠው የዘርፉ መሪ ስራ አስፈጻሚ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2) የዘርፉ መሪ ስራ አስፈጻሚ ለቀረበው ቅሬታ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
3) የዘርፉ መሪ ስራ አስፈጻሚ በሰጠው ምላሽ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለሚኒስቴር ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
4) የሚኒስቴሩ ጽ/ቤት ለቀረበው ቅሬታ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

5) በሚኒስቴሩ ጽ/ቤት ለቅሬታው የሚሰጠው ምላሽ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 29. የአገልግሎት ክፍያ

ማንኛውም ኦፕሬተር በዚህ መመሪያ መሠረት በየደረጃው የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት በመንግሥት የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

## 30. አባሪ ሰነዶች

ከዚህ መመሪያጋር የተያያዙ ሰነዶችና ቅጾች የዚህ መመሪያአካል ናቸው፡፡

## 31. የተሻሩ መመሪያዎች

1) የንግድ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች አደረጃጀት፣ ብቃት ማረጋገጫና የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 35 / 2013በዚህመመሪያተሽሯል፡፡
2) በመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት ለተሰማሩ ማኅበራት የተዘጋጀ የተሻሻለ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 690/2013 በዚህመመሪያተሽሯል፡፡
3) ይህንን መመሪያ የሚቃረኑ ማናቸውም ልማዳዊ አሰራሮችና ሌሎች መመሪያዎች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

## 32. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝበሚኒስቴሩ ሊያሻሻል ይችላል፡፡

## 33. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በዌብ ሳይት ላይ ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር)**

**የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**

## ሠንጠረዥ "ሀ"

**የደረቅ ጭነት ድንበር ተሻጋሪ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች ዝቅተኛ የሰው ኃይል አደረጃጀት**

| ተ.ቁ | የስራ መደብ | አክሲዮን ማኅበር | | | ኃ/የተ/የግ/ማኅበር | | | የግል ትራንስፖርት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሶስት | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሶስት | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሶስት |
| 1 | ዋና ሥራ አስኪያጅ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 2 | የኦፕሬሽንና ገበያ ጥናት ሃላፊ | 1 | 1 | - | 1 | - | - | - | - | - |
| 3 | የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ | 1 | 1 | 1 | - | - | - | - | - | - |
| 4 | የሒሳብ ባለሙያ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 5 | የኦፕሬሽንና ዕቅድ ባለሙያ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | - | - | - | - |
| 6 | የመንገድ ደኅንነት ባለሙያ | 1 | 1 | 1 | - | - | - | - | - | - |

## ሠንጠረዥ "ለ"

## ለሁሉም የኦፐሬተር ዓይነቶች ተፈላጊ የሰው ኃይል፣ የትምህርት ደረጃ፣ የትምህርት ዓይነት እና የሥራ ልምድ፡-

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መግለጫ | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት | የስራ ልምድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዋና ሥራ አስኪያጅ | ፒኤችዲ<br>ማስተር<br>ዲግሪ | በትራንስፖርት ፕላኒንግና ማኔጅመንት ወይም በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ኢንጅነሪንግ ወይም በአርባን ትራንስፖርት ወይም በትራንስፖርት ሳይንስ ወይም በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በሊደርሺፕ ወይም በሎጂስቲክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | 0/2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ |
| 2 | የኦፐሬሽንና ገበያ ጥናት ሃላፊ | ፒኤችዲ<br>ማስተር<br>ዲግሪ<br>ዲፕሎማ | በትራንስፖርት ፕላኒንግና ማኔጅመንት ወይም በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ኢንጅነሪንግ ወይም በትራንስፖርት ኦፐሬሽን ወይም በአርባን ትራንስፖርት ወይም በትራንስፖርት ሳይንስ ወይም በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በሊደርሺፕ ወይም በሎጂስቲክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በማርኬቲንግ ወይም በአካውንቲንግና ፋይናንስ ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | 0/2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ |
| 3 | የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ፡ | ማስተር<br>ዲግሪ<br>ዲፕሎማ | በኢኮኖሚክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በማርኬቲንግ ወይም በአካውንቲንግ ወይም በአካውንቲንግና ፋይናንስ ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | 0/2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ |
| 4 | የሂሳብ ባለሙያ | ማስተር<br>ዲግሪ | በአካውንቲንግ ወይም በአካውንቲንግና ፋይናንስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ | 0/2/4 ዓመት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዲፕሎማ | ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በባንኪንግና ፋይናንስ ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | እና ከዚ በላይ |
| 5 | የኦፐሬሽንና ዕቅድ ባለሙያ፡ | ማስተር ዲግሪ ዲፕሎማ | በትራንስፖርት ፕላኒንግና ማኔጅመንት ወይም በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ኢንጅነሪንግ ወይም በትራንስፖርት ኦፕሬሽን ወይም በአርባን ትራንስፖርት ወይም በትራንስፖርት ሳይንስ ወይም በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በሎጂስቲክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | 0/2/4 ዓመት እና ከዚ በላይ |
| 6 | የመንገድ ደኅንነት ባለሙያ፡ | ማስተር ዲግሪ ዲፕሎማ | በትራንስፖርት ፕላኒንግና ማኔጅመንት ወይም በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ኢንጅነሪንግ ወይም በትራፊክ ኢንጅነሪንግ ወይም በትራንስፖርት ኦፕሬሽን ወይም በአርባን ትራንስፖርት ወይም በትራንስፖርት ሳይንስ ወይም በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ ወይም በኢኮኖሚክስ ወይም በቢዝነስ አስተዳደር ወይም በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በማኔጅመንት ወይም በሳይኮሎጅ ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | 0/2/4 ዓመት እና ከዚ በላይ |

## ሠንጠረዥ "ሐ"

## የሥነ-ምግባር ጉድለቶች እና የአስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድ

### 1) በዕርከን አንድ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚያስወስዱ የጥፋት ዓይነቶች

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች ዝርዝር | ለጥፋቱ የተሰጠው ክብደት |
|---|---|---|
| 1. | አፐሬተሩ አስፈላጊ መረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ አደራጅቶ አለመያዝ እና ሲጠየቅ ትክክለኛ መረጃ ወቅቱን ጠብቆ አለመስጠት | 7 |
| 2. | አፐሬተሩ አድራሻ ሲቀይር በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አለማሳወቅ | 8 |
| 3. | ጭነት ያልጫነን ተሽከርካሪ የጭነት ውል ወይም የጭነት ማዘዣ ሳይኖረዉ ወደ ወደብ እንዲሄድ ማድረግ፣ (የተላከ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ) | 20 |
| 4. | ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ባወጣዉ የደረጃ መስፈርት መሰረት የድርጅቱን ስም፣ አድራሻ እና አርማ የያዘ ስቲከር በተሽከርካሪዎች በሁለቱም ጎን አለመለጠፍ | 15 |
| 5. | ማንኛውንም ጭነት ህጋዊ ውል እና የጭነት ማዘዣ ሳይኖረው ማጓጓዝ | 20 |
| 6. | የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ መቆጣጣሪያ መሳሪያ ብልሽት ሲገጥመው አለማሳወቅ እና አለማስተካከል፣ | 15 |
| 7. | ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ በሚሆኑበት ጊዜ ያለማሳወቅ፣ | 15 |

2) **በዕርከን ሁለት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚያስወስዱ የጥፋት ዓይነቶች**

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች ዝርዝር | ለጥፋቱ የተሰጠው ክብደት |
|---|---|---|
| 1. | የድርጅቱን የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለመከታተል የተዘረጋውን ሥርዓት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለመቆጣጠር በሚያስችለው መልኩ 24 ሰዓት ክፍት አለማድረግ፣ | 5 |
| 2. | አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወቅቱን ጠብቆ አለማደስ፤ | 3 |
| 3. | በወደብ ላይ፣ በሀገር ውስጥ እና በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ጭነትን በአስቸኳይ ለማንገዝ በሚፈለግበት ጊዜ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጥ ኮታ ድልድል መሰረት አለመስራት፣ | 7 |
| 4. | የሌላ ድርጅት አርማና ስቲከር በተሽከርካሪዎች ላይ ለጥፎ መገኘት | 10 |
| 5. | ለሕገ ወጥ የሰዎች ዝዉዉር ተባባሪ መሆን እና ስደተኞችን በተሽከርካሪው ደብቆ ማጓጓዝ | 15 |
| 6. | የኮንትሮባንድ እቃ ማጓጓዝ፣ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት ወይም ወደ ጎረቤት ሀገር ይዞ መግባት፣ | 15 |
| 7. | የጫነዉን ጭነት በጥራት ወይም በብዛት ማጓደል ወይም በጫነዉ ጭነት ላይ ባዕድ ነገር በመቀላቀል የዕቃዉን ጥራት እንዲጓደል ማድረግ፣ | 10 |

| | | |
|---|---|---|
| 8. | የድርጅቱ አሽከርካሪዎች ወይም ወኪሎች በአድማ ላይ መተባበር ወይም ለአድማ ሌሎችን በማነሳሳት ተግባር ላይ መሳተፍ | 15 |
| 9. | በንግድ ያልተመዘገበ ተሽከርካሪን ወደ ንግድ ሥራ ወይም ወደ ኪራይ ማሠማራት፣ | 7 |
| 10. | ባልተመዘገቡ፣ የብቃት ማረጋገጫ ባልወሰዱና ባላደሱ ወይም በታገዱ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት መስጠት፣ | 5 |
| 11. | ትክክለኛ ያልሆኑና ሀሰተኛ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መላክ፣ | 8 |

# ሠንጠረዥ “መ”

## <u>የድርጅቱ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መመዝገቢያ ቅጽ /በድርጅቱ የሚሞላ/</u>

**የድርጅቱ ስም ------------------------**

| ተ.ቁ | የመኪና የሠሌዳ ቁጥር | የሞተር ቁጥር | የመኪና ሻንሲ ቁጥር | የተሳቢ. ሰሌዳ ቁጥር | የተሳቢ. ሻንሲ. ቁጥር | የስሪት ዘመን | | የመጫን አቅም በኩንታል | | ጠቅላላ ድምር በኩንታል | ጅፒኤስ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የጎታች መኪና | የተሳቢ. | የጎታች መኪና | የተሳቢ. | | | |
| 1. | | | | | | | | | | | | |
| 2. | | | | | | | | | | | | |
| 3. | | | | | | | | | | | | |
| 4. | | | | | | | | | | | | |
| 5. | | | | | | | | | | | | |
| 6. | | | | | | | | | | | | |